የ፳፻፪ ትክክለኛ ምርጫ ልሣን
ምርጫው በቸኸው ክፍል ተዘጋጅቷል።
ሕዝቡ ያለውዴታው ይሣተፋል።
የእኛም አስተዋፅዖ እነሆ።

# እስከመቼ

ጥር ፲፮ እስከ ጥር ፳፪ ቀን ፳፻፪ ዓ. ም.
January 24 to January 30, 2010
ቅፅ ፩ ቁጥር ፩
Volume I Number 1

## የምሁሩ ድርሻ

በዚህ ርዕስ አሁን እየተደረገ ያለውን ተመልክተን፤ ወደፊት መደረግ አለበት የምንለውን እንጠቁማለን። ባሁኑ ሰዓት የተማረው ክፍል፤ በድርጅት ዙሪያ ያለም ይሁን ከድርጅቶች ውጪ የሆኑ፤ ጥሩ ትንታኔዎችንና የገዢውን ቡድን የአስተዳደር ጉድለት እየደጋገሙ በፅሑፍ እያቀረቡልን ነው። መልካም።

የኢትዮጵያዊያን ድህረ ገፆችን ከምንጎበኘው ኢትዮጵያዊ መካከል ስንቶቻችን ነን ጊዜ ኖሮንና ጊዜ ወስደን አጣጥመን የምናነበው? ይህስ የሚደረገው በሥራ ሰዓት ነው ወይንስ በዬቤታችን ስንገባ?

ስለኢሕአዴግና ስለመለስ ዜናዊ ፀረ-ኢትዮጵያ ተግባር ስንት ጊዜ ይፃፋል? የፅሑፎችን የመጨረሻ ግብ ምንድን ነው? ፅሑፎቹ መደምደሚያቸው ምን ይላል?

እንደዕውነቱ ከሆነ የትንታኔው ሰዓት አልፎ የተግባሩ ጥሪ ከተደወለ ውሎ አድሯል። ካሁን በኋላ የሚመጡ ፀሐፊዎች ትግሉን ለሌሎች ትተው የታጋዮችን ታሪክ አቅራቢዎች፣ ለወደፊቱ መጪ ትውልድ የሀገሪቱን ወቅታዊ የፖለቲካ ትርምስ አዋጂዎች፣ እና ባሁኑ ሰዓት ታዛቢዎች ናቸው። በዕርግጥ ይኼንን ሚና የሚጫወቱ ምሁራን ትውልዳችን ይፈልጋል። እኛ የምንጠቁመው ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ከነኚህ ይልቅ ንቁ ተሣታፊዎችን ትውልዳችን የበለጠ መጠየቁን ነው።

## ያሁኑ ፖለቲካ

አሁን ዞረን ስንመለከት፤ የ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. እንቅስቃሴ የቅርብ ሩቅ ነው። ከሀገራችን የታሪክ ሂደት አንፃር ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. በጣም ቅርብ ነው። ይህ ቅርበት ደግሞ አሳሳች ነው። ሩቅ ነውና።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በ፹ ሚሊዮን ዙሪያ ይገመታል። የዚህ ክፍል ይበልጡ ወገን የተወለደው ከ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. ወዲህ ነው። ይህ የሚነግረን፤ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያን የሚያውቃት በደርግና በኢሕአዴግ ዘመን የተሣለችውን ኢትዮጵያ መሆኑን ነው። ይህ ነው የ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. እንቅስቃሴን ሩቅ የሚያሰኘው። ቀደም ብለን ከሀገር የወጣንም ሆነ በቅርብ የመጣንና በያለንበት ሀገር ያለውን የፖለቲካ ነፃነት የተላበስን ኢትዮጵያዊያን መገንዘብ ያለብን፤ የወቅቱ ፖለቲካ በዚህ አዲስ ኢትዮጵያዊ ዓይን መታየት ያለበት መሆኑን ነው።

የወቅቱ ፖለቲካ በኢሕአደግ የታሠሩ የፖለቲካ እስረኞችን ማስፈታት፣ ተቆርሶ ለሱዳን የተሠጠውን የድንበር መሬት ማስመለስ፣ ለውጭ ሀገር የንግድ ተቋሞች እየተሸነሸነ በመታደል ላይ ያለውን ያገራችን ለም መሬት ማስቆም፤ ኢሕአዴግ ያዘጋጀው የመሞሸሪያ ምርጫ፤ የትግሉ አንድ ገፅታ ነውና፤ ከኢሕአዴግ ሌላ አሸናፊ ባይታሰብም ሕዝቡ ዕድሉን ለትግሉ መጠቀሚያ ያደርገዋልና መታገያ ማድረግ ነው።

## የ፩ኛና የ፪ኛ ደረጃ ጥያቄዎች

አሁን በተያዝነው የፖለቲካ መንፈስ፤ ጉዟችን አድካሚና ውጤቱ የማይጨበጥ ነው። ይልቁንስ ያለውን ተጨባጭ ሁኔታ ተገንዝበን ለግቦቻችን ቅደም ተከተል አበጅተን መጓዝ መንገዳችንን ቀና ያደርገዋል። እናም አሁን ያዘልናቸውን የመታገያ ነጥቦች በሚከተለው ፈርጀናቸዋል።

፩ኛ ደረጃ ጥያቄዎች፤

- የፖለቲካ እስረኞች ይፈቱ
- ነፃ ምርጫ ይኑር
- የሕዝብ ድምፅ ይከበር
- ደንበራችን ይመለስ
- መሬታችን ለባዕዳን አይሠጥ

፪ኛ ደረጃ ጥያቄዎች፤

- የዴሞክራሲ መብት ይከበር
- ያለሕዝቡ ተሣትፎ የተደረጉ ውሎች ይሠረዙ
- የኤርትራ ጉዳይ የፖለቲካ መፍትሄ ይሠጠው

## ፩ኛ መልዕክት

ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ፤ በአሁኑ ሰዓት ሆነ ለወደፊቱ አስተማማኝና ሕጋዊ መንግሥት መመሥረት አስተማማኝነት፤ የሰፊው ሕዝብ ተሳትፎ የግድ ነው። እርስዎ ባሉበት ድርጅትም ሆነ በግለሰብ፤ የዚህ ተሣትፎ አካል ይሆኑ ዘንድ <u>እስከመቼ</u> ጥሪዋን ታቀርብልዎታለች። ይህ ሊተገበር የሚቻለው፤ በአንድ የፖለቲካ ድርጅት ጥረትና ጉብዝና ሣይሆን ሁላችንም የዬድርሻችን በምናበረክትበት መድረክ ነው። እናም ይተባበሩን።

## ፪ኛ መልዕክት

ውድ ኢትዮጵያዊ ሆይ፤ ይኼንን በሚያነቡበት ጊዜ ብዙ ሃሳብ በአዕምሮዎ እንደሚመላለስ ጥርጥር የለንም። ገፋፍቶዎት አጠር ያለ መልዕክት ወይንም ተግባር ጠቋሚ ፅሑፍ ሊቸሩ ከከጀለዎ እሰየው እንላለን። መልዕክትዎን ለማስተናገድ እንሞክራለን።

eske.meche@yahoo.com

ETHIOPIA